# የጡት ካንሰርን ለማከም መታየትና መገኘት ያለባቸው ሁኔታዎች

## General overview: Finding and Treating Breast Cancer

የጡት ካንሰር እንዳለብሽና እንደሌለብሽ ለማወቅ ብዙና የተለያዩ የሙከራ ምርመርዎችን ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ ይህንን ምርመራ ለማድረግ ብዙ ሳምንታትን ሊወስዱ ይችላሉ።



*Image: National Cancer Institute; Bill Branson, Photographer*

ስክሪኒንግ ቴስትስ (Screening tests) ጤነኛ ሴቶች የበሽታውን ምልክት እንዳለባቸውና እንደሌለባቸው የተለመደ ወቅታዊ ምርመራ ማድረግ ይኖርባቸዋል። ይህንን ምርመራ ማናቸውም ጤነኛ የሆኑ ሴቶች በተወሰነ ጊዜ ተከታትለው መመርመር ይኖርባቸዋል። ለምሳሌ ሶስቱ ዓይነት የሙከራ ምርመራዎች እንደሚከተሉት ናቸው። አመታዊ ሜሞግራም በሐኪምሽ የሚታይ በጅ በመዳሰስ የሚደረግ ምርመራ እና የራስሽን ጡት በእጅሽ በመንካት የመመርመር ዘዴ ነው። ከነዚህም ምርመራዎች አንዱም እንኳ የታወከ ውጤት ካለው ወይም ምርቀዝ ከተገኘበት ሐኪምሽ ተጨማሪ ምርመራ (diagnostic) እንዲደረግ ያዛል።



*© 2005 Terese Winslow, U.S. Govt. has certain riahts*

ዳይጎኖስቲክ ምርመራዎች (Diagnostic tests) በሕመም ስሜቶች ምክንያት የጡት ካንሰር መኖሩ ከተጠረጠረ የሚደረግ ምርመራ ነው። አንደኛው የዲያግኖስቲክ የምርመራ ዓይነት ኤምአርአይ ነው። ይህም ኢ.ምአርአይ ማግኔትንና ኮምፒተርን በመጠቀም የውስጥ ሰውነትን አጥርቶ የሚያሳይ መሳሪያ ነው። የደም ምርመራና የአጥንት ማንሻ (Bone scan) ደግሞ ሌላ ሁለት ተጨማሪ የዲያግኖስቲክ መመርመርያ ዘዴዎች ናቸው። እንዲሁም ሜሞግራምና አልትራሳውንድ እንደዚሁ የተለያዩ የዲያግኖስቲክ መመርመሪያዎች ናቸው።



*© 2005 Terese Winslow, U.S. Govt. has certain rights*

ካንሰር እንዳለሽና እንደሌለሽ እርግጠኛ ለመሆን የተለያዩ የቀዶጥገና አሰራርን በመጠቀም ትንሽ ቲሹ ቆርጦ በማውጣት በመመርመር ካንሰር እንዳለና እንደሌለ ለማወቅ ይረዳል። ከላይ የተጠቀሱት የቀዶ ጥገና ውጤትና ሐኪምሽ ከዚህ ቀጥሎ ምን እርምጃ መውሰድ እንዳለበሽ ያስገነዝብሻል። አብዛኛውን ጊዜ ባዮፕሲው መጀመርያ ከተደረገ በኋላ ቀጥሎ ቀዶ ጥገና በማድረግ ካንሰሩንና አካባቢውን ቲሹ እንዲወገድ ይደረጋል። በተጨማሪ በዚሁ ቀዶ ጥገና ጥቂት የሊምፍ ኖዶችንም በማውጣት እግረመንገዱን በዲያግኖስቲክ ምርመራ ያልታየውን ምን ያህል ካንሰሩ ካለበት ቦታ አልፎ እንደተዛመተ ለማወቅ ያስችላል። በላምፔክቶሚ ቀዶ ጥገና የካንሰሩን ምርቀዝና (lump) በአካባቢው ያሉትን ቲሹዎች የሚያስወግድ ነው። ማይሴክቶሚ ቀዶ ጥገና ማለት ደግሞ ሙሉ የጡቱን አካል ቆርጦ ማውጣት ማለት ነው።

ተጨማሪ ቀዶ ጥገና ካላስፈለገ ሌላ የተለየ ተጨማሪ ሕክምና ያስፈልግ ይሆናል። የጨረራ (Radiation) ሕክምና ሁልጊዜ ሳይሆን አንዳንዴ ሊያስፈልግ ይችላል። የላምፔክቶሚ ቀዶ ጥገና ከተደረገ ካንሰሩ ወደቀረው ጡት ቲሹዎች እንዳይመለስ ለመከላከል ግዴታ የጨረራ (Radiation) ሕክምና መስጠት ይኖርበታል። እንዲሁም በጣም ላደገና ለተባዛ ካንሰርና ብዙ የሊምፍ ኖዶች ካንሰራማ ከሆኑ የጨረራ (Radiation) ሕክምና አስፈላጊ ይሆናል።



*Image: National Cancer Institute*

በምርመራው ቀዶ ጥገና ወቅት ካንሰር እያለ ሳይወገድ ከቀረ አንቺን የሚያክሙሽ የሕክምና ቡድን በሌላ መንገድ ሕክምናው እንዲሰጥሽ ያዛሉ። ከዚህ ቀጥሎ የተጠቀሱት የተለመደ የሕክምና አሰጣጥ ዓይነቶች ናቸው። እንደሚታወቀው ካንሰርን በቀዶ ጥገና ማስወገድ ተቀዳሚ አሰራር ነው። ነገር ግን ኪሞቴራፒ (Chemotheraphy) ከዚህ ህክምና ጋር አብሮ የሚሰጥ ከሆነ ቀዶ ጥገናው በሁለተኛ ደረጃ ይሰጣል ማለት ነው። ከዚያም ጨረራ (Radiation) ከቀዶ ጥገናው አስከትሎ ይሰጣል። እንዲሁም ኪሞቴራፒ የሚሰጥ ከሆነ አስከትሎ ጨረራ (Radiation) ይሰጣል። እነዚህ የሕክምና ዓይነቶች ከተሰጡ በኋላ ታሞክስፌን (Tamoxifen) ወይም ሌሎች የሆርሞን ቴራፒ ሕክምናዎች ይሰጣሉ።



*Image: National Cancer Institute*

አንዳንዴ ጊዜ ቀዶ ጥገና ከመደረጉ በፊት ሲቶችና ሐኪሞቻቸው የሚያስከትለውን ውጤት ለማየት የተለየ የሕክምና አሰጣጥ ዘዴ ይከተላሉ። ያም ሆነ ይህ ካንሰሩ ግን ምንጊዜም መወገድ ይኖርበታል። ያደገና በጣም በማደግ ላይ በሽታ ላለባቸው ሴቶች ግን መጀመሪያ ኪሞቴራፒ (Chemotheraphy) መስጠት አስፈላጊ ይሆናል። ቀዶ ጥገና ከመደረጉም በፊት ኪሞቴራፒ ያደገን የካንሰር እጢ ለማሟሸሽና በሰውነት ውስጥ የተሰራጨውን ካንሰር ለመዋጋት ይረዳል። አንዳንዴ የሕክምና ማዕከሎች ኪሞቴራፒንና ጨረራን (Radiation) ለያይተው ሳይሆን ባንድነት ይሰጧቸዋል።